# Learning by Ear 2013

መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE SIXTEEN: በአንበሳው ዋሻ

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Ludger Schadomsky**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE ONE: አቶ ጃለታ AND FAMILY HAVING LUNCH AT HOME**

- **አቶ ጃለታ (M, 45)**
- **ወ/ሮ ዘውዲቱ(F, 35)**
- **ንጉሴ (M, 16)**

**SCENE TWO: ምህረት IN ዳንኤል'S ROOM**

- **ዳንኤል (M, 16)**
- **ምህረት (F, 15)**
- **በለጠ (M, 15)**

**SCENE THREE: ብሩክ AND ቅዱስ BEG IN OUANGO**

- **ብሩክ (M, 8)**
- **ቅዱስ (M, 8)**
-

## 1. INTRO - NARRATOR:

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ተከታታዮች። ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ የሚቀርበው ድራማ 16 ኛ ክፍል ነው። የዛሬው ርዕስ «በአንበሳው ዋሻ » ይሰኛል። እስቲ ለመነሻ እንዲሆነን የሰሞኑን መለስ ብለን እንቃኝ።

ምንም እንኳን በወንዶች ማደሪያ ሴት ተማሪዎች እንዳይገቡ በጥብቅ የተከለከለ ቢሆንም ዳንኤል ምህረትን እንድትመጣ ጠይቋታል። እሷም ይህን በተመለከተ የተሰማትን ስጋት ለቅርብ ጓደኛዋ ትዕግስት ነግራታለች።

2. ምህረት (EP 15, 79): በጣም ነው የፈራሁት። ቅር ላሰኘው አልፈልግም። በሌላ በኩል ደግሞ ነገሩ ልክ አይደለም። ምን ባደርግ ይሻላል ትያለሽ?

3. ትዕግስት (LINE 84): እኔ አንቺን ብሆን ኖሮ እዚህ ቤተ መፅሀፍት ተቀምጬ እያነበብኩ ራሴን አልበጠብጥም ነበር።

ስለሆነም ምህረት የተሰማትን ስጋት ሁሉ ትታ ዳንኤልን ለማግኘት ወደ ወንዶች ተማሪዎች ማደሪሪያ አምርታለች።ይህም እቤት የገጠማትን ችግር ሸሸት ይመስለል። እናቷ ወ/ሮ ሉሊት የምህረት አባት በመጨረሻ የተወለደውን ህፃን ከሸጡ በኋላ ከሰዋቸው ተጣልተው ከቤት ሸሸተዋል። እንዲሁ አክስታቸው ዘንድ ጎረቤት ሀገር ያድጉ የነበሩት መንታ ልጆች ባልታወቀ ምክንያት ከቤት መጥፋታቸውንም ወ/ሮ ሉሊት ሰምተዋል።

4. አቶ ሙላቱ (EP 12, 42): "ሉሊት ለፖሊሶቹ ምንድን ነው ያልሻቸው?

5. ሉሊት: " ብሩክ እና ቅዱስ እንደጠፉ ብቻ ነው የነገርኳቸው። ደስ አለህ?

6. አቶ ሙላቱ (LINE 56): "ሉሊት ከማንጋ እየተነጋገርሽ እንደሆነ ብታስታውይ ጥሩ ነው። አሁንም ቢሆን ባለቤትሽ ነኝ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ንጉሴ ከት/ቤት ሲመለስ መጥፎ ነገር ገጥሞታል። እናቱ እቤታቸው ውስጥ የፍጥኝ ታስረውና ንብረታቸው ተዘርፎ ነበር። ፖሊሶችም እስካሁን ሌቦቹን አላገኟቸውም። የአቶ ጃለታ ቤተሰብ

የገጠመውን ችግር እንዴት ይወጣ ይሆን? ቤተሰቡ በሙሉ ምሳ ለመብላት ገበታ ቀርቧል። እንከታተል።

**SCENE ONE: አቶ ጃለታ AND FAMILY HAVING LUNCH AT HOME**

**7. SUBURB ATMO, MIDDAY**

**8. SFX: SOUNDS OF PEOPLE EATING LUNCH, CUTLERY ETC.**

**9. አቶ ጃለታ:** **(trying to break the silence)** እሺ ንጉሴ፤ ትምህርት እንዴት ነው?

**10. ንጉሴ:** ትምህርት አሪፍ ነው አባዬ።

**11. SFX: MORE CUTLERY SOUNDS**

**12. ወ/ሮ ዘውዲቱ:** **(bitterly)** እስካሁን ድረስ ለምንድን ነው ፖሊሶቹ ሌቦቹን ያልያዙት? ቀናት አልፈዋል፤ ሆኖም እስካሁን ምንም የሰማነው ነገር የለም።

**KW BEGIN**

**13. አቶ ጃለታ:** **(politely)** እርግጠኛ ነኝ የተቻላቸውን ሁሉ እያደረጉ ነው። መከታተልና እና የማጣራት ስራዎች እኮ ብዙ ጊዜ ይወስዳሉ። እንኳን አንቺ ብቻ ደህና ሆንሽልን የንጉሴ እናት።

**14. ወ/ሮ ዘውዲቱ:** **(with pain)** እንኳን አንቺ ደህና ሆንሽ? ምን እያልክ ነው? እንዴት ፈርቼ እንደነበር የምታውቀው ነገር አለ? አሁን እንኳን ድንጋጤው አለቀቀኝም። ሊገሉኝ ሁላ እኮ ይችሉ ነበር።

**15. አቶ ጃለታ:** **(sighing heavily)** አዎ አውቃለሁ ይገባኛል የንጉሴ እናት። ግን ተርፈሻል አልተገደልሽም። በህይወት እና በደህና ሁኔታ ላይ ነሽ። የምደሰተው ለዚህ ነው።

**16.** ንጉሴ: አሁን ስለሌላ ነገር ልንወያይ እንችላለን? ስለ ሞትና ዘረፋ ማውራት በጣም ይጨንቃል።

**17.** አቶ ጃለታ: እውነትህን ነው። እስማማለሁ። ይህንን ትተን ህይወታችንን መምራት መቀጠል አለብን።

**18.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(hits back)** እናንተማ ምንም ስላልደረሰባችሁ እዚህ ተቀምጦ ይህን ማለቱ አይከብዳችሁም። በገመድ ተጠፍንጎ እና ጎሮሮ ላይ ጩቤ ተደቅኖ፤ ነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ ማለት ምን እንደሆነ አልደረሰባችሁም።

**KW END**

**19.** አቶ ጃለታ: **(concerned)** ግን የኔ ውድ። አሁን ምንም ልናደርግ የምንችለው ነገር የለም። መፍትሄው የሚመጣው ከፖሊሶቹ ነው። ወንጀለኞቹን አሁንም እየፈለጉ ነው።

**20.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: እየፈለጉ! ኡኡቴ። እኔ ራሴ ይህንን ዘረፋ ያሴረው ሰው ዘንድ ልወስዳቸው እችላለሁ።

**21.** አቶ ጃለታ & ንጉሴ: **(shocked reaction)**

**22.** አቶ ጃለታ: **(excited)** ፊታቸውን አይተሻል እንዴ ታስታውሺያቸዋለሽ? ሌቦቹ እነማን እንደነበሩ ታውቂያለሽ ማለት ነው?

**23.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: የለም። እንዳልኩት ሰዎቹ ጭንበል አጥልቀው ነበር ። ይሁንና በጉዳዩ የማን እጅ እንዳለበት ለመገመት አያዳግተኝም።

**24.** አቶ ጃለታ: ማነው? ንገሪን! ልባችንን አታንጠልጥያት።

**25.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: የቀድሞው ዘበኛችን ያ ሰካራም ሙላቱ ነዋ !

**26.** ንጉሴ: **(utterly shocked)** በፍፁም እማዬ። እንዴት እንደዚህ ታስቢያለሽ? አቶ ሙላቱ እኮ የምህረት አባት ናቸው።እንደዚህ ያለ ስራ አያደርጉም።

**27.** አቶ ጃለታ: ንጉሴ ደሞ አንተ ምን ታውቃለህ? **(pondering the idea).** የንጉሴ እናት እውነትሽን ሊሆን ይችላል። እንዴት እሱን ሳልጠረጥር ቀረሁ? በመጀመሪያ ነገር ስራውን ያለምንም ምክንያት አቋረጠ ከዛ ደግሞ ከጥቂት ቀናት በኋላ እኛ ተዘረፍን።

**28.** ንጉሴ: ግን እማ ድምፁን ታስታውሻለሽ?

**29.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(defensively)** የለም አይ አላስታውስም። ነገር ግን ይህ ሰው የዕለት እንቅስቃሴዎቻችን ማወቅ አለበት። መቼ ከቤት እንደምንወጣና እንደምንገባ በትክክል ያውቃል ማለቴ ነው።

**30.** ንጉሴ: **(surprised)** አባዬ በፍፁም እንዳትሳሳት አቶ ሙላቱ ከዚህ ጉዳይ ጋ ር የሚያገናኛቸው ምንም ነገር አይኖርም።

**31.** አቶ ጃለታ: አይሆንም። እስኪ አስበው፤ እንዴ! ሙላቱ በዚህ ዘረፋ ላይ ተሳትፎ ይሆናል። በጣም እርግጠኛ ነኝ የሴራው አካል ሳይሆን አልቀረም።

**32.** ንጉሴ: እኔ ይህን አልሰማም። ሁለታችሁም የምትሉትን ስለማልቀበለው ማዳመጥ አልፈልግም።

**33. SFX: CHAIR BEING PUSHED BACK**

**34.** አቶ ጃለታ: **(orders)** ንጉሴ በል ተቀመጥ እና ምግብህን ጨርስ።

**35.** ንጉሴ: ወደ ክፍሌ መሄድ እፈልጋለሁ።

**36. SFX: FOOTSTEPS WALKING AWAY**

**37.** አቶ ጃለታ: **(sighs)**

38. ወ/ሮ ዘውዲቱ: እና ታድያ ስለ ጉዳዩ ምን ለማድረግ አሰበህል?

39. አቶ ጃለታ: ምን የንጉሴን ወይንስ የሙላቱን ?

40. ወ/ሮ ዘውዲቱ: የ ሙላቱን ነው እንጂ አንተ ደግሞ። ንጉሴን ተወው ። እሱ ገና ልጅ ነው።

41. አቶ ጃለታ: ጥሩ! ለግዜው ምን እንደማደርግ አላውቅም። ያለ ማስረጃ ላሳስረው አልችልም። ስለእሱ የበለጠ ለማወቅ እሞክራለሁ። የሆነ ነገር እንዳገኘሁ ለፖሊስ አሳውቃለሁ።

42. ወ/ሮ ዘውዲቱ: ግን ተጠንቀቅ ጃለታ።...ሙላቱ አደገኛ ሰው ሊሆን ይችላል።

43. አቶ ጃለታ: አያሳስብሽ። በአደጋን ውስጥ እንዴት ማለፍ እንደሚቻል አውቅበታለሁ።

44. **MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE TWO: ምህረት IN ዳንኤል'S ROOM</u>**

45. **SFX: ዳንኤል TIDIES UP HIS ROOM (THINGS MOVED, STEPS), LOCKER DOOR OPENS AND CLOSES**

46. **SFX: GENTLE KNOCK ON DOOR**

47. ዳንኤል: ማነው? ቆዩኝ አንዴ...

48. **SFX: DOOR CREAKING OPEN**

49. ዳንኤል: **(pleasantly surprised)** ታድያስ ምህረት! እንዴት የሚያስደስት ነገር ነው። ይሳካል ብዬ አልጠበኩም ነበር። ግቢ፣ ግቢ ...

50. ምህረት: **(unsure of herself)** ታድያስ... እንዴት ነህ? እሺ ምኑጋ ልቀመጥ?

51. ዳንኤል: የፈለግሽበት ቦታ ላይ። ቆይኝ አንዴ በሩን ልቆልፈው።

52. **SFX: CREAKING DOOR BEING CLOSED**

53. ዳንኤል: እንደዚህ ይሻላል አይደል?

54. ምህረት: እኔንጃ… እርግጠኛ አይደለሁም።… እሺ እንደዚህ ነው የምትኖረው?

55. ዳንኤል: እ - አዎ እንዲህ ነው፤ ክፍሌን አልወደድሽውም እንዴ? ከመምጣትሽ በፊት ጠብ እርግፍ እያልኩ ሳፀዳ ነበር። **(clears throat)** ለምን ብትይ አንቺ ልዩ እንግዳዬ ስለሆንሽ ነው።

56. **SFX: PATTING THE BED**

57. ዳንኤል: ነይ እዚህ ጋ አረፍ በይ። ዘና በይና አሪፍ ሰዓት እናሳልፍ።

58. ምህረት: ጓደኛህ በለጠ እንዴት ነው? እክፍልህ ይሆናል ብዬ አስቤ ነበር ።

59. ዳንኤል: በለጠ ደህና ነው። ልክ ነሽ ጊዜውን እዚህ ማሳለፍ ይወዳል። አሁን ግን እዚህ የለም። እንዴት ነሽልኝ ምህረትዬ? የተጨነቅሽ ትመስያለሽ።

60. ምህረት: አይ… ይቅርታ… ልክ አንበሳ ዋሻውስጥ የገባሁ ያህል ተሰምቶኝ ነው። **(laughs a little)**

61. ዳንኤል: **(gentle laugh)** ቀልደኛ ነሽ። እና አንበሳው ማን ነው? እኔ እንዳልሆን ብቻ!

62. ምህረት: እኔንጃ አላውቅም። እዚህ መምጣት አይገናኝም ነበር ዳንኤል። ምቾት አይሰማኝም።

63. ዳንኤል: ምናልባት ሙዚቃ ለችግሩ መፍትሄ ይሆናል። ቆይ አንዴ ጠብቂኝ። … **(stretches out to press play)**

64. **SFX: BED SQUEAKING**

**65. SFX: BUTTON PRESSED**

**66. SFX: SMOOTH MUSIC PLAYS IN BACKGROUND**

**67.** ዳንኤል: ይሄው! እንዴት ነው ወደድሸው? ዘና ያደርጋል? ይሄን ሙዚቃ በየቀኑ አዳምጠዋለሁ። …አንቺን በጣም ነው የሚያስታውሰኝ።

**68.** ምህረት: **(giggles)** ትቀልዳለህ? እንዴት አድርጎ ነው እኔን የሚያስታውስህ?

**69.** ዳንኤል: መንፈስን የሚያረጋጋ እና የሚያዝናና ነው። ልክ እንደ አንቺ።

**KW BEGIN**

**70.** ምህረት: ዳንኤል ይኼን ሁሉ የት ነው የተማርከው እባክህ?

**71.** ዳንኤል: **(caught off guard)** እ? ምኑን? የምትይው አልገባኝም።

**72.** ምህረት: ስለሁሉም ነገሮች። ዘና ስላለው ሙዚቃ፣ ስለ ምርጡ አነጋገር፣ ዘበኛው እንዴት ሹልክ አድርጎ ወደ ክፍልህ እንዳስገባኝ እማ አይነሳ። ይሁን ሁሉ ማን ነው ያስተማረህ?

**73.** ዳንኤል: በቃ በአንቺ እብድ በማለቴ ነው። እንደውም እውነቱን ልንገርሽ። ሆሊውድ ነው።

**74.** ምህረት: **(shocked)** ሆሊውድ? አሜሪካ ያለው? ሆሊውድ ሄደህ ነበር እንዴ? ይህንን አልነገርከኝም ነበር።

**75.** ዳንኤል: **(bursts out laughing)** የለም ምህረት! ማለቴ አንዲት ውብ ልጅን እንዴት አድርጎ መንከባከ እንደሚገባ ከሆሊውድ ፊልሞች ተምሬያለሁ። በነገራችን ላይ ፊልም ትወጃለሽ? የቅርብ ጊዜ ፊልሞች በሙሉ አሉኝ።

**76.** ምህረት: **(still shocked)** ዳንኤል! ት/ቤት ሆነህ ፊልሞች ታያለህ? ክልክል እኮ ነው።

77. ዳንኤል: አውቃለሁ። ግን ምን አስጨነቀኝ።

**KW END**

78. ዳንኤል: ምህረት ነይ እጎኔ ተቀመጪ። እስካሁን ቆመሽ ነው ያለሽው። እስኪ እጄን ያዢኝ።

79. ምህረት: ዳንኤል በእውነት ላምንህ እፈልጋለሁ። ግን በጣም ነው የፈራሁት። ምን ማድረግ እንዳለብኝ ግራ ገብቶኛል። መንፈሴ ተመሰቃቅሏል። ከዚህ በፊት እንደዚህ ተሰምቶኝ አያውቅም።

80. ዳንኤል: እመኚኝ ምህረት። በፍፁም አላስቀይምሽም ወይንም አልጎዳሽም። በቃ እዚህ ስለተገናኘን በጣም ነው ደስ ያለኝ። ትመጫለሽ ብዬ አልገመትኩም ነበር። እጅሽን ስጪኝ። ቅር አይበልሽ። እዚህ ያለነው ሁለታችን ብቻ ነን። ሁሉንም ቀስ እያልን ነው የምናደርገው። በኔ ይሁንብሽ።

**81. SFX: ምህረት'S FOOTSTEPS CAUTIOUSLY MOVING CLOSER**

**82. ዳንኤል:** **(proudly)** አዎ! አሁን እዚህ አጠገቤ ተቀመጪ።

**83. SFX: RAPID KNOCKING ON DOOR**

**84. ምህረት:** **(reacts in fear)** አይሆንም። ወይኔ ዳንኤል ምን ይሻለኛል?

**85. ዳንኤል:** **(curses)** ማነው?

**86. በለጠ:** **(behind the door, in panic)** በለጠ ነኝ። ቀይ ካርድ! ቀይ ካርድ!

**87. ምህረት:** ቀይ ካርድ?ምን ማለቱ ነው?

**88.** ዳንኤል: ቀይ ካርድ ማለት የትምህርት ቤት ኃላፊዋ እየመጡ ነው ለማለት እንደ ማስጠንቀቂያ የምንጠቀመው ነው። አልፎ አልፎ ኋላፊዋ ማደሪያ ክፍሎቻችንን ለማየት ይመጣሉ። ቶሎ በይ ከዚህ በፍጥነት መውጣት አለብን።

**89. SFX: BED SQUEAKING AS ዳንኤል GETS UP**

**90. SFX: FOOTSTEPS RUSHING TO THE DOOR**

**91.** ዳንኤል: ከኋላዬ ተሸሽገሽ ቁሚ። ችግር የለም ምህረት

**92. SFX: CREAKING SOUND OF DOOR OPENING**

**93. FOOTSTEPS RUSHING OUT OF THE ROOM INTO THE CORRIDOR**

**94. MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE THREE: ብሩክ AND ቅዱስ BEG IN OUANGO</u>**

**95. SFX: BUSY STREET ATMO… COINS JINGLING IN METAL CAN**

**96.** ቅዱስ: ስለ ማርያም… እርዱን አባካችሁ (To ብሩክ) ብሩክ ብርድ እና ርሃብ ሊገለኝ ነው።

**97.** ብሩክ: እኔስ ብትል ቅዱስ። ቢሆንም ልመናችንን ማቋረጥ የለብንም። አለበለዚያ በርሃብ መጠበሳችን ነው። ደግሞ እዚህኦአንጎ የሚባል ቦታ ብርዱ አይጣል ነው።

**KW BEGIN**

**98.** ቅዱስ: ወደ ወርቅ ማዕድን ቦታው ብንሄድ ሳይሻል አይቀርም። ቢያንስ እዛ ምግብ አለ።

**99.** ብሩክ: አይሆንም። እንዴት እንደደበደቡን ታስታውሳለህ አይደል? በዚያ ላይ የሰራው ከባድነትን አሰበው። ወደ ኪ.ሲ.ምባ ብንሄድ ይሻላል። እማ፣ አባዬ እና ምህረት ናፍቀውኛል።

**100.** ቅዱስ: እኔንም ብሩክ። ግን እንዴት ነው የምንጓዘው? አክስቴ ለምለም ብቻ ናት ልትወስደን የምትችለው። እዚህ ያሉት ሰዎች ቋንቋችን እንኳ አይገባቸውም፤ ለመርዳትም ፍቃደኞች አይደሉም።

**KW END**

**101.** ብሩክ: የሰፈራችንን ስም «ታንዲካ» እያልን ብንጠራ ሳይሻል አይቀርም። የታንዲካ ጎስቋላ መንደርን የማያውቅ የለም፤ ኪ.ሲ.ምባ እንደሆነ ለማንም ግልፅ ነው።

**102.** ቅዱስ: አዎ ጥሩ ሀሳብ ነው። በል እንሞክር…

**103.** ቅዱስ/ ብሩክ: «ታንዲካ»! «ታንዲካ»! «ታንዲካ» ለመጓዝ ገንዘብ ቸግሮን ነው እባካችሁ እርዱን …

**104. SFX: COINS BEING DROPPED IN CAN**

**105. MUSIC THEME INTERLUDE**

**106. OUTRO - NARRATOR:**

በዚሁ መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ በሚል ርዕስ የሚቀርበውን የበማድመጥ መማር ድራማ 16ኛ ክፍል እናጠናቅቃለን። የምህረት ወንድሞች እቤታቸው የሚያደርሳቸው በቂ ገንዘብ ያገኙ ይሆን ወይንስ አክስታቸው ወ/ሮ ለምለም አስቀድማ ፈልጋ ታገኛቸዋለች? በዳንኤል ክፍል ደግሞ ቀይ ማስጠንቀቂያ በርቷል። ከምህረት ጋር እያለ የት/ቤቱ ኃላፊ ይይዙት ይሆን? የሚቀጥለው ክፍል እንዳያመልጣችሁ። ይህንን እና ሌሎች ክፍሎችን ደግመው መስማት ከፈለጉ dw.de/lbe የተሰኘዉን ድረ- ገፃችን ይጎብኙ፤ አልያም በፌስቡክ አድራሻችን ላይ ይከታተሉ። እስከሚቀጥለዉ ጊዜ፤ ጤና ይስጥልን።